# ተጨባጭ የኢትዮጵያ ሁኔታ
# እኛን ኤርትራውያንንም ይመለከተናል


ተስፋጽዮን መድሃኔ

(ፕሮፌሰር)

ብረመን ዩኒቨርሲቲ፣ ጀርመን



ብረመን፡ መጋቢት 2016

# ማብራሪያ

ይህ የሚከተለው ጽሑፍ እ.አ.አ በጥር 30 ቀን 2016 ዓ.ም በፍራንክፈርት ከተማ፣ ጀርመን አገር፡ ግንባር ሃገራዊ ድሕነት ኤርትራ ባዘጋጀው ሰሚናር የተላለፈ መልእክት ነው፡፡ ይህ መልእክት እኔ እንደ ግለ ሰብ ያሰተላለፍኩት ነው፡፡ መልእክቱ እንዲተላለፍ የገፋፋ ወይም የጠየቀ አንድም ድርጅት ይሁን እንቅስቃሴ የለም፡፡ ስለዚህ ይዘቱን ይሁን ስርጭቱን በሚመለከት ሓላፊነቱ ሙሉ ለሙሉ የኔ ብቻ መሆኑን ለማሳወቅ እወዳለሁ፡፡

በኤርትራ የተቃውሞ ጐራ ውስጥ የዚህ መልእክት ይዘት አዲስ፣ የአቀራረቡ መልክ ደግሞ ቀጥተኛ በመሆኑ ብዙ ያገር ልጆች ደስ እንደማይላቸው መገመት እችላለሁ፡፡፡ ላንዳንዶቹማ እስካሁን ይዘዋቸው እየተጓዙ የቆዩትን አስተያየቶችና ግምቶች ካለምህረት የሚገዳደር ስለሆነ መጀመሪያ ላይ ቀልባቸውን አዛብቶ ትንሽ የሚረብሻቸው ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ እኔ ይህንን መልእክት ማስተላለፌ ተገቢ ነው፡፡ እኔ ኤርትራዊ በመሆኔ ይህንን አስተያየት መግለጽ መብቴ ነው፡፡ በዚህ መብት ለመጠቀም የማንም ሰው ወይም መንግስት ፈቃድ እንደማያስፈልገኝ አሰምርበታለሁ፡፡ በተጨማሪ ደግሞ ህግንና ፖለቲካን በሚመለከቱ የእውቀት መስኮች — በተለይ ህገ መንግስትን፣ ዴሞክራሲንና ሰብአዊ መብቶችን በሚመለከት፣ - በተለያዩ ደረጃዎች የረዥም ዓመታት ተሳታፊ በመሆኔ፡ ይህን መልእክት ለማስተላለፍ ሞያዊ ሓላፊነትም እንዳለብኝ አንባቢዎችና አድማጮች ታሳቢ እንዲያደርጉልኝ ለማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡

ይህን መልእክት አዘጋጅቼ እንድጨርስ እውነተኛ የአገር መንፈስና ተቆርቋሪነት ያላቸው ኤርትራውያን በተለያዩ መልኮች አበረታትተውኛል፣ ተባብረውኛል፡፡ በጣም አመሰግናቸዋለሁ፡፡

ይህ ፅሑፍና በፍራንክፈርት የተደረገው ንግግር በይዘት አንድ ናቸው፡፡ ይህን ፅሑፍ ለማሳተም በምዘጋጅበት ጊዜ በጣም ጥቂት፡ በይዘቱ ትርጉም ላይ ፈፅሞ ለውጥ ያላስከተሉ የቃላትና የሃረጎች ለውጦች ተደርገዋል፡፡

የዚህ መልእክት ይዘት እስከ ጥር 30 ቀን 2016 በነበሩ ግኝቶችና እድገቶች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

ይህንን ፅሁፍ ከትግርኛ ወደ አማርኛ ለተረጐሙት አገር-ወዳድ ኢትዮጵያውያን ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡

ተስፋጽዮን መድሃኔ
ብረመን፣ መጋቢት 2016

# ተጨባጭ የኢትዮጵያ ሁኔታ እኛን ኤርትራውያንንም ይመለከተናል

ተስፋጽዮን መድሃኔ (ፕሮፌሰር)
ብረመን ዩኒቨርሲቲ
ጀርመን

አስቀድሜ ከፍ ያለ ሰላምታዬን ለዚህ ሰሚናር ተሳታፊዎች አቀርባለሁ፡፡ ከጥቂት ሳምንታት በፊት የዚህ ሰሚናር አዘጋጆች በሰሚናሩ እንድገኝ በቃልና በጽሑፍ ጥሪ ላኩልኝ፤ ጥሪው አጠር ያለ መልእክት እንዳስተላልፍ የሚያስታውስ ይዘትም ነበረው፤ በዛ መሰረት ይኸው አቋም- አዘል የሆነ አጭር አስተያየት ለማስተላለፍ እፊታችሁ እገኛለሁ፡፡ ለሰሚናሩ አዘጋጆች ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በችግር ላይ ያለ ፖለቲካዊ ድርጅት የሚያካሂደው ሰሚናር ተራ መድረክ አይደለም፡፡ የህዝቡ፣ አገሩና አካባቢው ሁኔታዎች በሚመለከት ያሉትን ችግሮችና ጥያቄዎች ቅንነት፣ ሳይንሳዊ እውነታና ወኔ መለያዎቹ በሆነ አቀራረብ ለማጣራት የሚዘጋጅ ውይይት ነው፣ ወይም መሆን አለበት፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአንድ ኤርትራዊ ተቃዋሚ ድርጅት የሚካሄድ ሰሚናር በእርግጥ እነዚህ ባህሪያት ሊኖሩት ይገባል፡፡

## ፩

በማስተላልፋቸው ሁሉም መልእክቶች ርእሱን ወይም አጀንዳውን የምመርጠው በድንገት አይደለም፡፡ እኔ የማደርገው፣ በጊዜው ጎልቶ የሚታየውን ወይም ባስቸኳይነቱና አስፈላጊነቱ የላቀና አከራካሪ የሆነ ጉዳይ የትኛው ነው ብዬ በመምረጥ ነው፡፡ የምታስታውሱ ከሆነ፡ በካስል ይሁን በሌሎች ቦታዎች ሳስተላልፋቸው የነበሩ መልእክቶች በተቻለ መጠን በወቅቱ መከሰት ይጀምሩ የነበሩትን ጉዳዮች የሚመለከቱ ነበሩ፡፡

እንግድያውስ አሁንም የመልእክቴ አጀንዳ የመረጥኩት በአሁኑ ጊዜ እኛንና አካባቢያችንን በሚመለከት መነጋገሪያና አካራካሪ የሆነው ጉዳይ ምንድን ነው ከሚል ጥያቄ በመነሳት ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ደረጃዎች የሚመለከቱን አገር ነክ፣ አካባቢያዊና ዓለም አቀፍ ድርጊቶችና እድገቶች አሉ፡፡ በኤርትራ፡ በኢትዮጵያ፡ በአውሮጳና በአመሪካ በይዘታቸው

እኛን — የኤርትራ ተቃዋሚ ሃይሎችን — የሚመለከቱ ገጽታዎች ያሏቸው ሁኔታዎችና ግኝቶች አሉ። ከእነዛ ሁኔታዎች ሁሉ ዛሬ ልናገርበት የመረጥኩት ጉዳይ በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ የኦሮምያ ቦታዎች ሲካሄዱ የሰነበቱት፣ አሁንም ገና በመካሄድ ላይ ያሉ እንቅስቃሴዎች፣ የአዲስ አበባ መንግስት ግብረ-መልስና እኛን ደግሞ እንዴት እንደሚመለከቱን ነው።

የምታስታውሱት ከሆነ፣ ባለፈው የካስል ፈስቲቫል (ማለት ነሓሴ 2015) የማንም መንግስት መሳሪያ መሆን እንደሌለብን አንስቼ እንደሚከተለው ብያችሁ ነበር።

*“የአዲስ አበባ መንግስት መሳሪያ መሆን የለብንም... ። የአዲስ አበባ መንግስት መሳሪያ መሆንህ ወይም አለመሆንህ እንድታውቅ ያ መንግስት በኢትዮጵያ ውስጥ ምን በማድረግ ላይ እንዳለ ማወቅ አለብህ፤ ይህን ለማወቅ ደግሞ የኢትዮጵያ ሁኔታዎች መከታተል አለብህ፡ የኢትዮጵያ ሁኔታዎች በጥልቀት መረዳት አለብህ ማለቴ ነው። ግልጽ አድርጌ ልናገር፡ የወያኔ መሳሪያ እየሆንክ እንዳለህ ወይም እንደሌለህ እንድታውቅ ወያኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ምን እያደረገ እንዳለ በዝርዝር ማወቅ አለብህ ማለቴ ነው።*

*ስለዚህ ሁላችሁም በተቃዋሚ እንቅስቃሴዎች ያላችሁ የኢትዮጵያ ሁኔታዎች በዝርዝር ተከታተሉ። የክትትላችሁ ዘዴ ደግሞ ነጻና የራስ ተነሳሽነት ያለው መሆን አለበት። ይህ ማለት፡ ያ መንግስት የሚሰጣቸውን መረጃዎች ማመን ሳይሆን ራሳችሁ ባደረጋችሁት ክትትል ኢትዮጵያ ውስጥ ምን በመካሄድ ላይ እንዳለ እወቁ ማለት ነው።" ብያችሁ ነበር።*

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያን ሁኔታዎች የሚከታተል ሁሉ በተለያዩ የኦሮሞ ክልል ቦታዎች ፈንድቶ የቆየና ገና አሁንም ሙሉ ለሙሉ ያልቆመው የህዝብ መነሳሳት ወይም እምቢተኝነት (ፖፑላር አፕራይዚንግ) ምን ያህል አሳሳቢ መሆኑ ለመረዳት አይቸግረውም። አሳሳቢ ከሆነ ዘንድ ለኤርትራዊያንም የሚያሳስቡ ገጽታዎች ሊኖሩት ይችላሉ እና ብንወያይበት መጥፎ አይደለም በማለት ይኸው "ተጨባጭ የኢትዮጵያ ሁኔታ እኛን ኤርትራውያንንም ይመለከተናል!“ በሚል ርእስ መልእክቴን አቀርባለሁ።

ተቃውሞው በአንዳንድ ቦታዎች ትንሽ ቢቀዘቅዝም፤ በመሰረቱ አልቆመም። ስለዚህ የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ መሰረታዊ ምክንያት ምን እንደነበረ፡ ከተነሳ በሁዋላ ደግሞ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የሰጠው መልስ ምን እንደነበረና መልሱ ምን መሆን እንደነበረበት መገንዘብ አስፈላጊ ነው። እነዚህ ግንዛቤዎች እኛ ኤርትራውያን

ተቃዋሚዎች ያሉንን መሰረታዊ ችግሮች በጥልቀት ለመረዳት ያግዙናል የሚል ድምዳሜ ያረካኛል፡፡

ወደ ኦሮሞ ጉዳይ ከመግባቴ በፊት፡ በሌሎች የኢትዮጵያ ቦታዎችም ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች እንዳሉ መጥቀስ እፈልጋለሁ፡፡ በወልቃይት-ጠገዴ፣ በጋምቤላ፡ በኡጋዴን፡ በበኒሻንጉል ጉሙዝ አልፈው አልፈው የሚነሱ ያሉት በመጠንና ጥንካሬ የተለያዩ ተቃውሞዎች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም፡፡ ዛሬ ወደ እነዚህ ጉዳዮች አልገባም፤ የእነዚህ ጉዳዮች አሳሳቢነት ሳላጣጥል በኦሮሞ ህዝብ ተነስቶ በሰነበተውና ገና በመቀጠል ላይ ባለው እንቅስቃሴ ላይ አተኩራለሁ፡፡

፪

ይህ የኦሮሞ ህዘብ እንቅስቃሴ ከሁለት ወር ተኩል በፊት፣- ማለት ብህዳር ወር አጋማሽ፣ የተጀመረ ነው፡፡ ቀውስ ሊያስከትል የሚችል ህዝባዊ እምቢተኝነት ነው፡፡ ይህን ጉዳይ በሚመለከት ሁኔታውን የሚከታተሉ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ አመሪካና የአውሮጳ ህብረት የሚገኙባቸው ትላልቅ መንግስታት፣ እንደ የተባበሩት መንግስታት የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ እንደ አምነስቲ፣ ሁማን ራይትስ ዎችና ፍሪደም ሃውስ ያሉ ዓለም አቀፍ የሰብኣዊ መብት ተሟጋቾች፣ በዓለም ደረጃ ታማኝነት ያላቸው ጋዜጠኞች ወዘተ የሚያሳስባቸው መሆኑን ገልጸው፣ ተቃውሟቸውን አሰምተው ምክሮቻቸውንም ለግሰዋል፡፡ የአፍሪቃ ህብረትም "የኦሮሞ ጉዳይ ብቅርብ እየተከታተልነው ነው" እንዳለ በ28 ጥር በአመሪካ ድምጽ ረድዮ ተገልጸዋል፡፡ መግለጫውን የሰጡት ዶክተር ዓይሻ ዓብዱላሂ የሚባሉ በአፍሪቃ ሕብረት የፖለቲካዊ ጉዳዮች ኮሚሽነር ናቸው፡፡ ዶክተር ዓይሻ የአፍሪቃ ሕብረት ጽሕፈት ቤትና የሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መናሃርያ የሆነችው ኢትዮጵያ ታላቅ አገር በመሆኗ ችግር ውስጥ እንዳትገባ የኦሮሞን ጉዳይ በሚመለከት ከመጋረጃ በስተጀርባ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶች በመካሄድ ላይ እንዳሉ በግልጽ አሳውቀዋል፡፡

የእንቅስቃሴው የቅርብ ጊዜ መነሻ የአዲስ አበባ ከተማ የመሬት አስተዳደር ለማስፋት የታቀደ ውጥን ለሚሟላት የተደረገ ዝግጅት ነው፡፡ ውጥኑ ከኦሮሞ ክልል መሬት ተቆርጦ ወደ አዲስ አበባ አስተዳደር እንዲገባ የሚያደርግ ነው፡፡

የእንቅስቃሴው መሠረታዊ ምክንያት ግን ዞሮ ዞሮ ባለፉት 25 ዓመታት ሲጠራቀም የቆየ ብሶት ነው፡፡ በአጭር አገላለጽ ይህ ህዝባዊ እምቢተኝነት የህወሓት መንግስት ስልጣን ከያዘ ጀምሮ ሲተገብረው የቆየና ገና እየተገበረው ያለ ዴሞክራሲ አልባው የዘውግ ፌደራሊዝም ያመጣቸው ችግሮች፡ በምርጫ መልክ የተሸፈነ አምባገነናዊ ስርዓት፣ የሰብአዊ

መብቶች ጥሰት፣ የሕግና ፍትሕ ጉድለት፣ ድህነት፣ ስራ አጥነት፣ ረሃብ፣ እንደዚሁም አድልዎና ሙሰኝነት መለያው የሆነ አስተዳደር ወዘተ ነው፡፡

ዘውጋዊ ፌደራሊዝም የኢትዮጵያ አንድነትን አላልተዋል፡፡ በቋንቋ ላይ በተመሰረተ ብሄረተ-ሰብነት አገሪቷን መከፋፈል፡ የዴሞክራሲ ጉድለት ተጨምሮበት፡ የኢትዮጵያ ህዝብን እየከፋፈለው ነው፡፡ ዳኛቸው አሰፋ የሚባሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና ፕሮፌሰር የነበሩ ከአዲስ አበባ ትንሽ ወጣ ብለህ ወደ ሌላ ክልል (ለምሳሌ ወደ ኦሮሞ ክልል) ብትገባ እንደ የውጭ ዜጋ ታይተህ፡ "ከየት ነው የመጣኸው?" ተብለህ እንደምትጠየቅ ይገልጻሉ[1]፡፡ አገር ወዳድ የሆኑት ዶክተር ዳኛቸው "ኢትዮጵያ አለች ወይ" ይላሉ፡፡አሁን የምናየው ለረጅም ጊዜ ጠማማ ትርጉም ተሰጥቶት አምባገነንትን ሲያገለግል የቆየው የብሄሮች መብት የሚል መርህ ካስከተለቻው ችግሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

ከአሁን በፊት የህወሓት-ኢህአዴግ መንግስት በምርጫ መልክ የተሸፈነ የአንድ ብሄረ-ሰብ ሰዎች የሚቆጣጠሩት አምባገነናዊ ስርዓት ነው ብያችሁ ነበር፡፡ አሁንም እደግመዋለሁ፡፡ የዚህ መንግስት ሁሉም ተቋሞች በህዝባዊ ወያኔ ቁጥጥር ስር ናቸው፡፡ እነዛ የኢህአዴግ አባሎች የሆኑ የሌሎች ብሄረ-ሰቦች ድርጅቶች ህወሓት የሚቆጣጠራቸው ናቸው፡፡ ህግ አውጪው አካል (ማለት ፓርላማ ወይም ምክር ቤት) በወያኔ-ኢህአዴግ ቁጥጥር ስር ነው፡፡ እንደምታውቁት አሁን አሁን በተለይ ደግሞ ምርጫውን ሁሉ የሚያሸንፈው ወያኔ ማለት ኢህአዴግ ነው፡፡ በ2010. 99,6% የፓርላማ ወንበሮች ኣሸነፉ፣ አሁን ደግሞ (ማለት በ2015) ወንበሮቹን 100% ኢህአዴግና በነሱ ቁጥጥር ስር የሆኑ የነሱ አጋሮች አሸነፉ፡፡ በምክር ቤቱ ውስጥ አንድም ተቃዋሚ የለም፡፡ የህግ አስፈጻሚ አካሉም እንደዛው የወያኔ የበላይነት ያለበት ነው፡፡ በመንግስቱ ውስጥ ዋናዎቹ ሚኒስተሮች የወያኔ አባሎች ናቸው፣ በይፋ የወያኔ አባሎች ካልሆኑ ደግሞ ከጠቅላይ ሚኒስተር ሃይለማርያም ደሳለኝ ጀምሮ ነፃነት (ማለት አውቶኖሚ) የሌላቸው የወያኔ ታዛዦች ናቸው፡፡ የውጭ ጉዳይ አስተዳደርና የፀጥታ ጉዳዮች አስተዳደርም ወያኔ-ኢህአዴግ የሚቆጣጠራቸው ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ወታደራዊ ሃይል ደግሞ ግልጽ በሆነ መልኩ ብህወሓት ቀጥጥር ስር ነው፡፡ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ጀኔራሎችና ኮሎኔሎች የወያኔ አባል የሆኑ የትግራይ ሰዎች ናቸው፡፡ በጣም የላቁ የወታደራዊ እዝ (ሲኒየር ኮማንድ ፖሰትስ) መሪዎች ከጀኔራል ሳሞራ የኑስ ጀምረው በሙሉ የወያኔ አባሎች ናቸው[2]፡፡

1 .ዳኛቸው ኣሰፋ “ኢትዮጵያ አለች ወይ?”

2 Keffyalew Gebremedhin, “Ethiopia promotes 37 senior officers to rank of generals; Tigreans are given most of it”, available online

ያገሪቷ ኢኮኖሚ በህወሓት-ኢህአዴግ ቁጥጥር ስር ነው፡፡ እነዛ ጀኔራሎችና ሌሎች ትላልቅ ባለ ኮከብ ወታደራዊ አዛዦችና ሲቨል ባለስልጣኖች ሃብት አካብቷል፡፡ ከዚህ ጋር የተያያዘ የሙስና ችግር ከባድ እንደሆነ የሚታመኑ ታዛቢዎች ይገልጻሉ፡፡ በትላልቅ ባለስለጣኖች የሚፈጸሙ የጉቦና ሌሎች ኣይነት የሌብነት ድርጊቶች ክፉኛ ተሰፋፍቷል፤ ስር ሰዷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በአገሪቷ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ድህነት እንዳለ ማንም የሚመሰክረው ነው፡፡ድህነት በትግራይም ሳይቀር አለ፡፡ እንዲያውም አብዛኛው የትግራይ ህዝብ በወያኔ ስርዓት እንደተጐዳ ታዋቂ የትግራይ ተወላጆች ይመሰክራሉ፡፡ ለምሳሌ በትውልዱ ከአድዋ የሆነ ዳዊት ገብረ-እግዚአብሄር የተባለ የተዋጣለት ባለ ሀብት (ኢንቨስተር) "የትግራይ ህዝብ ከሌሎች የበለጠ ጥቅም ያገኛል የሚል አባባል አለ፤ መሰረት ያለው አባባል ነው?" ተብሎ በአንድ ቃለ መጠይቅ ሲጠየቅ "ማንም ሰው የመሰለውን ሊያወራ ይችላል፡፡ግን አይቶ ነው ያወራው ወይስ በአሉባልታ ነው? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ የትግራይ ህዝብ የስርዓቱ ተጠቂ እንጂ ተጠቃሚ አይደለም፡፡" ብሎ መልሷል[3]፡፡ እንደዚሁም ፡ ቋንቋቸው አማርኛ የሆነ ታዋቂው ኢትዮጵያዊ ምሁር፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም "የወያኔ ጥላቻ ፍሬ" በሚል ጽሁፋቸው፡ በወያኔ ስርዓት የተጠቀሙ የትግራይ ሰዎች በጣም ጥቂት መሆናቸውን ገልጸው ከመሰከሩ በሁዋላ፡ ወያኔ በሚፈጽማቸው ድርጊቶች ሁሉንም የትግራይ ተወላጆች መክሰስ ትልቅ ስህተት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ እንዲያውም ብዙ የትግራይ ተወላጆች በአዲስ አበባ ለማኞች ሆነው እንደሚኖሩ፡ አንዳንዶቹ ሲለምኑ በማንነታቸው እየተሰደቡ የሚሳቀቁና የሚሰቃዩ መሆናቸው ይገልጻሉ[4]፡፡

በኢትዮጵያ የሰብኣዊ መብቶችን መረገጥ በሚመለከት ብዙ ተጽፏል፡፡ እኛ ትኩረታችን በኢሳያስ መንግስት በሚፈጸሙ የመብት ረገጣዎች ላይ ብቻ ስለሆነ ሌሎች ሁኔታዎችን ስለማናስተውል ነው እንጂ የወያኔ-ኢህአዴግ መንግስት የሚፈጽማቸው የመብት ረገጣዎች ብዙና ከባድ ናቸው፡፡ በብዙ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎች፡ የሰብኣዊ መብት ተሟጋቾች፡ ጋዜጠኞች ወዘተ ላይ ግፍ ደርሷል፡፡ ስንት እንደተገደሉ፡ ስንት ታስረው እንዳሉ፡ ስንት በሚደርሱባቸው ተጽእኖዎች በስቃይ ላይ እንዳሉ ብዙ ተጽፏል፡፡ ለምሳሌ ያህል የወያኔ መንግስት ብዙ ጋዜጠኞችን አስረው ካሉት መንግስታት ውስጥ አንዱ ነው[5]፡፡

3 .ዳዊት ገብረ እግዚኣብሔር፡ "የትግራይ ሕዝብ የሥርዓቱ ተጠቂ እንጂ ተጠቃሚ አይደለም" (ቃለ መጠይቅ)

4 መስፍን ወልደማርያም፡ "የወያኔ ፍሬ ጥላቻ" (ethiopiazare.com)

5 European Parliament, Joint Motion for a Resolution, RC\ 1084072EN.doc, (20, 1. 2016) available online

እንግዲያውስ በኦሮሚያና በተለያዩ ሌሎች የኢትዮጵያ ቦታዎች ፈንድቶ የሰነበተውና ባንዳንድ ቦታዎች ገና በመቀጠል ላይ ያለው እንቅስቃሴ ምንጩ ስገልጻቸው እንደቆየሁት የነገድ/ዘውግ አድልዎ፣ የሰብኣዊ መብቶች ጥሰት፣ አስተዳደራዊ ብልሹነት፣ የሰፊው ህዝብ ድህነትና የመከራ ኑሮ ሁኔታዎች ያስከተሉት ብሶት ነው[6]፡፡

## ፫

በኦሮምያ የተከሰተው መነሳሳት ወይም እምቢተኝነት በጣም የተቀጣጠለው የአዲስ አበባ መንግስት ችግሩን በውይይትና በመግባባት በመፍታት ፈንታ እንቅስቃሴውን በጉልበት ለመጨፍለቅ እርምጃዎች ስለወሰደ ነው፡፡ ሰራዊቱ በጭፍን በተማሪዎችና በሌላው ህዝብ ላይ ተኰሰ፣ በዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችን ደበደበ፣ ተማሪዎችን ኢላማ አድርጎ ገደለ፣ ብድብቅ ህይወት የመቅጨት ድርጊቶች ፈጸመ፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችንና ጋዜጠኞችን አሰረ፡፡ መንግስት አዲስ አበባን የማስፋት እቅዱ እንዳይተገበር ማስቆሙን ቢገልጽም የጉልበት እርምጃዎቹ ግን ቀጠሉ፡፡ የሰብኣዊ መብት ተሟጓቾች እንደሚሉት እስከ አሁን ድረስ ከ140 ወይም ከ150 የሚበዙ ሰዎች ተገድሏል[7]፤ በሺዎች የሚቆጠሩም ታስረዋል፡፡ እነዛ እንደነ አግአዚ ያሉ የሰራዊት አባሎች ከኦሮሞ ውጭ የመጡ ነበሩ፡፡ በዚህ ምክንያት የኢህአዴግ አባል የሆነው የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) የሃይል እርምጃውን ስለተቃወመው ከወያኔ መሪዎች ጋር ያለመግባባት ሁኔታዎች አስከትለዋል፡፡

የአመሪካ መንግስት የህወሓት-ኢህአዴግ ደጋፊ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ሂስ ለማሰማት ተገዷል፡፡ የአዲስ አበባ መንግስት ገምቢ ውይይት በማካሄድ ቅሬታዎቹን መፍታት አለበት በማለት በግልጽ ቋንቋ ትእዝብቱንና አቋሙን ገልጿል[8]፡፡

የአውሮጳ ህብረት በበኩሉ እንደ አመሪካ የወያኔ-ኢህአዴግ ደጋፊ ቢሆንም፣ በዚህ ሁኔታ ወያኔ-ኢህአዴግን አጥብቆ ወቅሷል፤ ምክር ቤቱ ከሁለት ሳምንት በፊት ገደማ ብዙ የአካባቢዎችና አለም አቀፍ ህጎችን በመጥቀስ ጠንካራ ሂሶች ያሉት ውሳኔ አሳልፈዋል፡፡ የኦሮሞ ህዝብ እንቅስቃሴ ሰላማዊ እያለ የመንግስት የፀጥታ ሃይሎች የጉልበት እርምጃዎች

---

6 ይህንን ሐቅ ብዙ ታዛቢዎቸ ጠቅሰውታል፡ ለምሳሌ አብርሃ በላይና አረጋዊ በርሄ ከጓዶቻቸው ጋር ባወጡት "ተዳጋጋሚ ጭፍጨፋዎች እንዲቆሙ አስጨፍጫፊዎች መወገድ አለባቸው፤ እኛም ኦሮሞዎች ነን" የሚል መግለጫ ይመልከቱ፡፡ ethiomedia .com

7 Mike A. “Decades Worth of Fear Has Turned Into Anger In Ethioipia”, ethiomedia.com January 11, 2016

8 .Messay Kebede, “TPLF in Disarray and the Remaking of National Unity”, ethiomedia.com, January 6, 2016

ወስደው ሰዎች በመግደላቸው፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችና ጋዜጠኞች በማሰራቸው፣ የተወሰኑትንም የቁም እስር አድርገው በመያዛቸው፡ ሃሳብን የመግለጽ መብታቸውን የተጠቀሙትን ፀሃፊዎችንና የሰላማዊ ሰልፍ ተሳታፊዎችን ጸረ ሽብር በሚል ሰበብ በሃይል በመደፍጠጣቸው፣ በኡጋዴንና በሌሎች የኢትዮጵያ ቦታዎች ሰብኣዊ መብቶች በመጣሳቸው ይወቅሳል[9]፡፡ ጋዜጤኞችን በሚመለከት ኢትዮጵያ በወያኔ-ኢህአዴግ ስር በዓለም በጣም ከከፉት የጋዜጠኞች አሳሪዎች ሆና፡ በአራተኛ ደረጃ መሆንዋ የአውሮጳ ህብረት ያሰምርበታል፡፡ እነዚህ በውሳኔው የተጠቀሱ ከገመናዎቹ የተወሰኑት ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት የአውሮጳ ምክር ቤት ተቃውሞውን በሃይል ለመጨፍለቅ የተወሰዱትን እርምጃዎች አውግዞ የአዲስ አበባ መንግስት ዴሞክራሲያዊና ሰብኣዊ መብቶችን የሚያጠቃልሉትን አለም አቀፍና የአካባቢ አዋጆችንና ህጎችን እንዲያከብር፣ ፀረ ሽብር ህጎችን የተቃዋሚ ፖለቲካዊ ሃይሎችን ለመጨቆን እንዳይጠቀምባቸው ያሳስባል፡፡ እንደዚሁም የአዲስ አበባ መንግስት ባለስልጣኖች (ወያኔ-ኢህአዴግ) ዘውጋዊና ሃይማኖታዊ አድልዎ እንዳያደርጉ፣ በተለያዩ ማሕበረ-ሰቦች ሰላማዊና ገንቢ ውይይት እንዲካሄድ እንዲያደርጉ ምክር ቤቱ ጥሪ አቅርበዋል[10]፡፡

በኢትዮጵያ በወያኔ-ኢህአዴግ ዘመን ተቃውሞ መነሳቱ አዲስ አይደለም፣ ካሁን በፊትም በአዲስ አበባ ይሁን በጋምቤላ ተቃውሞ ነበር፡፡ የአሁኑ ግን አሳሳቢ በሆነ መጠን ከቀድሞው ይለያል፡

1. ለምሳሌ ይህ እንቅስቃሴ በቀላሉ ሳይጨፈለቅ ለረዥም ጊዜ ቀጠለ፡ በተለያዩ ቦታዎችም ገና በመቀጠል ላይ ይገኛል፡፡
2. እንቅስቃሴው የተካሄደውና በመካሄድ ላይ ያለው በዋናነት ገጠር ላይ ነው፣ የወያኔ-ኢህአዴግ መንግስት ደግሞ ገጠር ዋናው ደጋፊያችን ነው ይላል[11] ፣
3. ቅራኔው በመንግስትና በህዝብ መካከል ነው እንጂ በመንግስትና በተወሰነ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት መካከል አይደለም[12]፣
4. በዚህ እንቅስቃሴ ምክንያት የኢህአዴግ ውስጣዊ አንድነት መላላት ጀምረዋል፣ ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት የኢህአዴግ አባል የሆነው ኦህዴድ የተወሰደውን የሃይል እርምጃ በመቃወም ከወያኔ መሪዎች ጋር ወደ አለመስማማት ገብቷል[13]፣

---

9. European Parliament, Joint Motion for a Resolution, RC/ 1084072EN.doc, (20, 1. 2016) available online
10. ዝኒ ከማሁ
11 Leenco Lata, "Time for Ethiopia's Ruling Party to Take Full Responsibility for its Failures", ethiomedia.com (December 28, 2015
12 . Nahome Freda, "No Government wins a War of Attrition with its own People", ethiomedia.com, (January 26, 2016)

5. ኢትዮጵያ በወያኔ ስር የተረጋጋች አገር ሆናለች የሚል አስተያየት ፈርሷል፡፡ ቀውስ ሊመጣ ይችላል የሚል ስጋት በምዕራባውያን መንግስታትና ኢንቨስተሮች ሳይቀር አለ[14] ፡፡
6. ግልጽና ከባድ ወቀሳዎች ከአመሪካና የአውሮጳ ሕብረት መንግስታት ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰምቷል፡፡
7. የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች ከብሄር ባሻገር አስበው በአገራዊነት መሰረት ሊተባበሩ እንደሚችሉ የሚጠቁሙ ምልክቶች ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ ባለፈው ሳምንት እነ ዶክተር አረጋዊ በርሄና የኢትዮሜድያ አዘጋጅ አብርሃ በላይ የሚገኙባቸው የትግራይ ሰዎች "እኛም ኦሮሞዎች ነን" የሚል ታሪካዊ አዋጅ ሊባል የሚችል መግለጫ አውጥተዋል[15]፡፡ የትግራይ ተወላጆች ብንሆንም የኦሮሞ ጭቆና ጭቆናችን ነው በማለት ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ወንድማማችነታቸውንና አንድነታቸውን ገልጸዋል፡፡

ይህና ይህን የመሰሉ ክስተቶች አዲስ ናቸው፡፡ በእርግጥም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች መተባበር አለባቸው የሚል ጥሪ ተሰሚነት እያገኘ መጥቷል፡፡

፬

ይህ የኢትዮጵያ ውስጣዊ ጉዳይ ነው፣ አይመለከተንም፣ የሚል አስተያየት ያላችሁ ልትኖሩ ትችላላችሁ፡፡ ይህ አስተያየት ግን የተሳሳተ ነው፡፡ አስቀድሞ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ አንድነት እየላላ ነው፡፡ ይህ መላላት እንደዛ ከቀጠለ ኢትዮጵያን እንዳይበታትናት ያሰጋል፡፡ ኢትዮጵያ ከተበታተነች ኤርትራም መበታተኗ አይቀርም፡፡ እንዲያውም የአፍሪቃ ቀንድ በሙሉ ይታመሳል፡፡ ስለዚህ እኛ ኤርትራውያን ለጥቅማችን ብለን የኢትዮጵያ አንድነት እንዲቀጥል እርዳታችንን ማበርከት አለብን፡፡በተጨማሪ ኢትዮጵያ ለአፍሪቃ፡ ከዛም በላይ ለሁሉም ጥቁር ህዝብ ታሪካዊ ሚና ያላት አገር ናት[16]፡፡ መበታተን የለባትም፡፡

---

13 . Messay Kebede, "TPLF in Disarray and the Remaking of National Unity", op. cit. See also, Hassen Hussein, "OPDO's Statement: a departure or business as usual", ethiomedia.com January 15, 2016
14. Messay Kebede, "TPLF in Disarray and ….", op. cit
15 . አረጋዊ በርሄና አብርሃ በላይ ከጓዶቻቸው ጋር ያወጡትን "ተዳጋጋሚ ጭፍጨፋዎች እንዲቆሙ አስጨፍጫፊዎች መወገድ አለባቸው፣ እኛም ኦሮሞዎች ነን" የሚል መግለጫ ethiomedia.com ይመልከቱ፡፡

መግለጫውን ያወጡት የትግራይ ሰዎች የሚከተሉት ናቸው፡፣ ኣብራሃ በላይ፡ ኣረጋዊ በርሀ (ዶር) በላይነሽ ተክለሃይማኖት፡ ገብረመድህን ኣርኣያ፡ ግደይ ኣሰፋ (ዶር) ግርማይ ገዛኸኝ፡ ካሕሳይ በርሀ፡ ነጋሲ በየነ፡ ተስፋይ ኣጽብሃ።
16 . የኢትዮጵያን ታሪካዊ ሚና በሚመለከት ብዙ ተፅፏል፡፡ ለምሳሌ በፕሮፌሰር ጳውሎስ ሚልኪያስና ፕሮፌሰር ጌታቸው መታፈርያ *"The Battle of Adwa: Reflections on Ethiopia's Historic Victory Against*

እንደዚሁም በኢትዮጵያ በብሄረ ሰቦች መካከል ሰላም መስፈን ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለኛ ለኤርትራውያንም አስፈላጊ ነው፡፡ በ2010 አንድ ግረጎሪ ስታንተን የሚባል አመሪካዊ ፕሮፌሰር በኢትዮጵያ ሁኔታ ላይ ጠቃሚ መግለጫ ሰጥቷል፡፡ ያተኮረበት ጉዳይ ሰብኣዊ መብቶችን የሚመለከት ነበር፡፡ በተለይ ጋምቤላን በሚመለከት የአዲስ አበባ መንግስትን ወቅሶ አንድ ከባድ ነገር ተናግሯል፡፡ ለስልጣን እና ሃብት አገሪቷን ጠፍረው የያዟት የትግራይ ሰዎች መሆናቸውን ከገለጸ በሁዋላ 'እኔ ለወደፊቱ ትግርኛ የሚናገረው ህዝብ እንዳይጠቃ እፈራለታለሁ' ብሏል፡፡ ሁኔታዎች ተለዋውጠው አመጽ ሲመጣ ትግርኛ የሚናገረው ሁሉ በሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሊጠቃ ይችላል የሚል መልእክት ነው ያሰማው[17]፡፡ ይህች ነጥብ በጣም አሳሰበችኝ፡፡ ለኢትዮጵያ ህዝብ ሁላችንም ትግርኛ የምንናገረው፡ ኤርትራውያን እንሁን የትግራይ ሰዎች፡ ሁላችንም "ትግሬዎች" ነን፡፡ እንደ ህዝብ በወያኔ ስርዓት ያልተጠቀምን እያለን፡ አደጋው ግን ለሁላችን ነው፡፡ እንግዲያውስ እንደዚህ ያለ አደጋ እንዳይመጣ ኢትዮጵያ ውስጥ የብሄረ ሰቦች ግንኙት በእኩልነት ላይ የተመሰረተና ሰላማዊ እንዲሆን እኛ ኤርትራውያን ለጥቅማችን ብለን እርዳታችንን ማበርከት አለብን፡፡

አሁን ያለው የህወሓት አካሄድ የሚያዛልቅ (ሳስተይናብል) አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ አሁንስ ወደ 100 ሚልዮን ገደማ ደርሷል፡፡ የትግራይ ህዝብ ከ6 ሚልዮን ትንሽ ቢበለጥ ነው፡፡ የትግራይ ህዝብ ከኢትዮጵያ ህዘብ 6,2% ነው፡፡ ታድያ 6,2 % ብቻ ሆነህ ኢትዮጵያን በቀጣይነት መቆጣጠር የሚቻል አይደለም፤ ቅንም አይደለም፡፡ ወያኔዎች በእርቅ አልፈው ወደ ዴሞክራሲና የእኩልነት ስርዓት ግንባታ የሚያደርስ መሰረታዊ ለውጥ ማድረግ እንዳለባቸው በ2008 ባሳተምኩት መጽሓፍ ገልጬ ነበር፡፡ አላደረጉትም፣ እንዲያውም ስልጣን ማጠቃለሉን አባባሱት፡፡ አሁንም በ2008 ያልኳትን እደግምላቸዋለሁ፡፡ ምንም ያህል እንኳን ባይሰሙም!

እኛ ኤርትራውያን ተቃዋሚዎች በኢትዮጵያ የተጀመረውን እንቅስቃሴ በሚመለከት እስካሁን ድረስ ያልነው የለም፡፡ ብዙ መንግስታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ስሞታቸውን እየገለጹ እኛ ዝም ስንል አያምርብንም፡፡ ለፍትሕና ለዴሞክረሲ በመታገል ላይ ያለን

---

*European Colonialism"* በሚል ርእስ የተዘጋጀ የድርሰት ስብስብ መጽሓፍ ይመልከቱ። በዚህ መጽሓፍ የሚከተሉት 3 ድርሰቶች ከዚሁ ፅሁፍ እርስት ጋር በበለጠ ይዛመዳሉ። Paulos Milkias, "The Battle of Adwa: The Historic Victory of Ethiopia over European Colonialism"; Negussay Ayele, "Adwa 1896: Who was Civilized and Who was Savage?"; Getachew Metaferia, "Ethiopia: A Bulwark against European Colonialism and its Role in the Pan-African Movement".

17 Gregory Stanton https://www.youtube.com/watch?v=vdvHC2PE-7c

በመሆናችን በኢትዮጵያም ይሁን በሌላ ቦታ የሚካየድ ፍትሓዊ ትግል ጉዳያችን ነው። ስለዚህም ተወያይተን ቅን እና ገንቢ ለምንለው አቋም የመንቀሳቀስ ሓላፊነት ያለን ይመስለኛል።

ህዝባዊ ወያኔን በሆነ መልክ የሚወቅስ አስተያየት ማሰማት ወይም አቋም መውሰድ የለብንም፡ ምክንያቱም ወያኔ ወንድሞቻችን ብቻ ሳይሆኑ ደጋፊዎቻችንም ናቸው ትሉ ይሆናል። ይህ አስተያየትም ብፍፁም የተሳሳተ ነው። አንድ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር አለ። በዓለም አቀፍ ደረጃ በሰብአዊ መብቶች ጥሰት የተከሰሰ አምባገነናዊ ስርዓትን በመቃወም ለዴሞክራሲ በመታገል ላይ ስላለን ማንም መንግስት እርዳታ እንዲሰጠን የተፈቀደ ነው፣ እንዲያውም ተገቢ ነው።ስለዚህ ወያኔዎች በእውነት እርዳታ አድርገውልን ቢሆን ኖሮ ግዳጃቸውን ነው የፈጸሙት እንል ነበር። ግን እኮ አልረዱንም። ሊረዱንም አይችሉም፣ በአገራቸው እንኳን — በተለይም ትግራይ ውስጥ- ዴሞክራሲንና ፍትሕን ያላሰፈኑ፣ እኛን ሊያግዙ!

የወያኔ መንግስት ትርጉም ያለው እርዳታ አላደረገልንም ብቻ ሳይሆን፣ በተጻራሪው አዳክሞናል!! እስከ አሁንም እያዳከመን ነው ያለው። ለምሳሌ እንደምታስታውሱት ታች አምና "ይኸውና!! ኤርትራ ሞተች። ትግል ለአገር ትንሳኤ" በሚል ርእስ ባቀረብኩት መልእክት ስለ ንጉስ ሲሲፉስ የሚነገረውን ግሪካዊ አፈ ታሪክ ጠቅሼ፡ ወያኔዎች እኛን በተደጋጋሚ የኛን የግንባሮችና እንቅስቃሴዎች ስብስብ እንዲደራጅ፣ ጥቂት ቆይተው ደግሞ እንዲፈርስ እያደረጉ ለስንት ዓመታት እያሽከረከሩ እንዳዳከሙን ገልጬ ነበር። እንደምታውቁት መጀመሪያ ምሕዝነት መጣች፣ ምሕዝነት ተበትና 4+1 መጣች፡ እሷ ተበትና ኪዳን ቁጥር 1 መጣች፣ ያች ኪዳን ተበትና ዳግማዊት ኪዳን መጣች፣ ያች ዳግማዊት ተዳክማ ደግሞ ኮሚሽን ሃገራዊ ዋዕላ መጣች፣ እሷም ሚሽሻ ባይቶ (ሽንጎ) የምትባል መጣች። "ባይቶም እንጃላት ጥሩ አካሄድ የምትሄድ ያለች አይመስልም፣ ከሷ በፊት የነበሩት ስብስቦች ያጋጠማቸው እድል ሳያጋጥማት አይቀርም።" ብያችሁ ነበር። ይኸውላችሁ እንግዲህ ከፈራሁት አላመለጥንም፣ ባይቶም ተዘጋች፣ ቁልፉን አስረክቡን ተባላችሁ።

እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ነገር አለ። በተቃዋሚ ድርጅቶች በኩል አንዳንድ ደክመቶች እንኳን ቢኖሩም ለተቃዋሚ ሃይሎቻችን መዳከም የላቀ ድርሻ የነበረውና ያለው የወያኔ መንግስት ነው። ወያኔዎች በየጊዜው በብሄር ይሁን በጎሳ ወይም በሆነ ሌላ መስመር ድርጅቶች እንዲገነጣጠሉና እንዲመሰረቱ እያደረጉ ጠንክረን እንዳንንቀሳቀስ አድርጓል። ከዘህ ሁሉ የባሰ ደግሞ እነዘህ ዋጋ የላቸውም ብሎው መውቀሳቸው ነው። ራሳቸው አዳክመውህ ሲያበቁ ደንታ ሳይሰጣቸው ዋጋ የለህም ብለው ይወቅሱሃል!!

አሁን ሁሉም ኤርትራውያን ተቃዋሚ ድርጅቶች ኢትየጵያ ውስጥ ትግልን በሚመለከት ትርጉም ያለው ህልውና የላቸውም፡፡ ትርጉም ከሌለው ህልውና ደግሞ ሌላ መንገድ መፈለግ የሚመረጥ ነው፡፡ ታጋይ ተስፋይ ተምነዎ ደጋግሞ የሚለውን እውነታ እንናገር፣ ኢትዮጵያ አሁን የትግል ቦታችን አይደለችም፡፡

አንድ አዲስ ነገር ካለ በቅርብ ጊዜ ያ "መድረኽ" የሚባለው እንቅስቃሴ ወደ አዲስ አበባ ገብቶ የክብር የሚመስል አቀባበል የተደረገለት መሆኑ ነው፡፡ እነዛ ምርጥ የመድረኽ መሪዎች በህዝባዊ ግንባር ወይም ህግደፍ የታወቁ ባለስልጣኖች የነበሩ በመሆናቸው ታሪካቸው ከወያኔ ጋር የሚያዛምድ ገጽታዎች አሉት፡፡ በዚያ ታሪክና በሌሎች ሁኔታዎች (ፋክተርስ) ምክንያት በዚሁ ጊዜ ከወያኔ ጋር መዛመዳቸው ድብቅ እቅዶች ያሉበት እንዳይሆን የሚያሳስብ ነው፡፡

ስላዳመጣችሁኝ በጣም አመሰግናችሁ አለሁ!!

# ዋቢ ሰነዶች

-. ዶር. ዳኛቸው አሰፋ፣ "ኢትዮጵያ አለች ወይ?" http://ethsat.com/.../esat-human-rights-interview-with-dr-da.../

-.. Keffyalew Gebremedhin, "Ethiopia promotes 37 senior officers to rank of generals; Tigreans are given most of it", 12 September 2012 (available online)

- ዳዊት ገብረ እግዚአብሔር፡ "የትግራይ ሕዝብ የሥርዓቱ ተጠቂ እንጂ ተጠቃሚ አይደለም" (ቃለ መጠይቅ): (Source The Reporter) *ethiomedia.com* – August 17, 2015

- መስፍን ወልደማርያም፡ "የወያኔ ጥላቻ ፍሬ": ሚያዝያ 2006 (ብአቄጻጽራ ግዕዝ) http://www.ethiopiazare.com/articles/opinion-2/3583-yeweyane-yeferhat-wetet-new-by-prof-mesfin-woldemariam

- European Parliament, Joint Motion for a Resolution, RC\ 1084072EN.doc, (20, 1. 2016) available online

- አብርሃ በላይና አረጋዊ በርሄ ከጓደቻቸው ጋር "ተደጋጋሚ ጭፍጨፋዎች እንዲቆሙ አስጨፍጫፊዎች መወገድ አለባቸው፣ እኛም ኦሮሞዎች ነን"፣ http://www.ethiomedia.com/1010ideas/egnam_oromowoch_nen.pdf

- Mike A. "Decades Worth of Fear Has Turned Into Anger In Ethiopia", *ethiomedia.com* January 11, 2016

- . Messay Kebede, "TPLF in Disarray and the Remaking of National Unity", *ethiomedia.com*, January 6, 2016

- Leenco Lata, "Time for Ethiopia's Ruling Party to Take Full Responsibility for its Failures", *ethiomedia.com* (December 28, 2015)

- Nahome Freda, "No Government wins a War of Attrition with its own People", *ethiomedia.com*, (January 26, 2016)

Hassen Hussein, "OPDO's Statement: a departure or business as usual", *ethiomedia.com* January 15, 2016

Gregory Stanton https://www.youtube.com/watch?v=vdvHC2PE-7c

Paulos Milkias & Getachew Metaferia, *The Battle of Adwa: Reflections on Ethiopia's Historic Victory Against European Colonialism* (New York: Algora Publishers, 2005)